


King County GIS CENTER

የሲያትል የወረዳ መልሶ ማከፋፈል ኮሚሽን የአቀረበው የከተማ ምክር ቤት ወረዳ ድንበሮች

# የወረዳ መልሶ ማከፋፈል:

## ከኅዳር 15 ቀን 2022 በፊት የቀረበው ካርታ ላይ አስተያየትዎን ይስጡ።

**1**

ኮሚሽኑ ለሚቀጥሉት 10 ዓመታት የከተማው ምክር ቤት ወረዳ ድንበሮች ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ የሚያሳይ ኦፊሴላዊ የካርታ ረቂቅ ፈጥሯል። አዲስ ድንበሮች እርስዎን በከተማ ምክር ቤት ውስጥ ማን እንደሚወክልዎ ተፅዕኖ ያደርጋል።

**2**

ነባር ያሉትን እና የታቀዱትን ድንበሮች ያወዳድሩ። በ2020 የሕዝብ ቆጠራ ላይ በመመስረት፣ የሲያትል ከተማ ከ2010 ጀምሮ በ21.1 ከመቶ አደገ። በህጋዊው መስፈርት* መሰረት እያንዳንዱ ወረዳ በ1% ውስጥ ተመሳሳይ አይነት የህዝብ ብዛት ሊኖረው ይገባል፣ ይህም ወደ 105,288 ይህል ነው።

* ከኋላ በኩል የበለጠ ያንብቡ

| ወረዳ | አሁን ያለው ህዝብ | የቀረበው ካርታ የሕዝብ ብዛት |
|---|---|---|
| 1 | 99,698 | 105,848 |
| 2 | 99,163 | 105,520 |
| 3 | 106,845 | 105,011 |
| 4 | 106,103 | 105,614 |
| 5 | 99,102 | 105,150 |
| 6 | 102,753 | 105,861 |
| 7 | 123,351 | 105,091 |

**3**

ኮሚሽነሮቹ በእነዚህ ጥያቄዎች ላይ የእርስዎን ግብረ መልስ መስማት ይወዳሉ:

- ሰፈርዎ የት ነው?
- የእርስዎ ሰፈር የጋራ ባህል፣ ባህሪያት፣ ወይም ትስስር አለው?
- የእርስዎ ሰፈርዎ ከከተማው መንግሥት ጋር ስላለው ግንኙነት ያስቡ። የወረዳው ድንበር ለውጦች እርስዎ ከእርስዎ ተወካዮች ጋር እንዴት እንደሚሰሩ ላይ ተጽእኖ ይኖረዋል?
- የወረዳው ድንበር ለውጦች ሰፈርዎን በምን ምን መንገዶች ይጠቅም ይሆናል?

ግብረ መልስዎን ለእኛ ለመላክ ይህን የምስጢር ምልክት (QR) ኮድ ይጠቀሙ።

**4**

**ስለ የወረዳ መልሶ ማከፋፈል ሂደት የበለጠ ይረዱ:**

- Seattle.gov/redistricting
- **ጥያቄዎች: ኢሜይል** elsa.batres-boni@seattle.gov

Seattle




King County GIS CENTER

ነባር የሲያትል ከተማ ምክር ቤት የወረዳ ድንበሮች

## የወረዳ መልሶ ማከፋፈል ደንቦች **:

- ወረዳዎች እርስ በርስ በተቻለ መጠን በሕዝብ ብዛት በቅርበት እኩል መሆን አለባቸው፤ ከሁሉ ትልቅ የሆነ ወረዳ የህዝብ ብዛት በጣም ትንሽ ከሆነ ወረዳ የህዝብ ብዛት ከአንድ ከመቶ በላይ [ከሁሉም ትንሹ ወረዳ ከሆነ የህዝብ ብዛት] መብለጥ የለበትም። ይህ ማለት እጅጉን ትልቅ የሆነ የወረዳ የህዝብ ብዛት በጣም ትንሽ የሆነ ወረዳ የህዝብ ብዛት ከ101% መብለጥ የለበትም።
- ወረዳዎች በተቻለ መጠን የታመቁ እና በመልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ የተሳሰሩ/ የተቀጣጠሉ እንዲሆኑ ተደርገው ድንበሮች ይሳላሉ።
- ወረዳዎች የተሸፋፈኑ መሆን የለባቸውም፣ እና የህዝብ ብዛት ውሂብ ማንኛውንም የዘር ቡድን ወይም የፖለቲካዊ ፓርቲ ለመደገፍ ወይም ለማጥላላት ምክንያት ጥቅም ላይ መዋል አይኖርበትም።
- አዲሱ የከተማ ምክር ቤት ወረዳ ድንበሮች በማንም ሰው የመኖሪያው ቤት ላይ የተመሰረቱ መሆን የለባቸውም። ካርታቸውን በሚስሉበት ጊዜ፣ የኮሚሽኑ እና የመልክአ ምድር መረጃ ባለሙያ (GIS) አማካሪዎች የማንኛውንም ሰው መኖሪያ ከግምት ውስጥ ማስገባት የለባቸውም።
- ተግባራዊነቱ በተቻለ መጠን፣ አዲስ ድንበሮች አሁን ያሉትን የወረዳ ድንበሮችን መከተል አለባቸው።
- መታየት በተቻለ መጠን ሁሉ፣ አዲስ ድንበሮች የታወቁ የውሃ መስመሮችን እና የሥነ መልክዐ-ምድር ድንበሮችን መከተል አለባቸው።
- በተቻለ መጠን ሁሉ፣ አዲስ ድንበሮች የሲያትል ማህበረሰቦችን እና ሰፈሮችን እንዳሉ ይጠብቋቸዋል።

** የከተማ ቻርተር ንዑስ ክፍል መ. ምክር ቤት የወረዳ መልሶ ማከፋፈል (3) እና RCW 29A.76.010(4)

# SEATTLE REDISTRICTING 2021-2023

